# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 2 ቁጥር 63 ህዳር 9 ቀን 2013ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## ‹‹ሕወሓት እስከ ዛሬ በታሪኩ ለእውነተኛ ድርድር እና ለእውነተኛ ንግግር ክፍት ሆና አያውቅም፡፡›› ኢዮብ መሣፍንት



# ቆይታ

## ‹‹ሕወሓት እስከ ዛሬ በታሪኩ ለእውነተኛ ድርድር እና ለእውነተኛ ንግግር ክፍት ሆኖ አያውቅም፡፡››ኢዮብ መሣፍንት

ኢዮብ መሣፍንት የዚህ ሳምንት የ‹‹ቆይታ›› አምድ እንግዳችን ናቸው፡፡ የኢዜማ ብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ናቸው፡፡ ኢዮብ ከሐረማያ ዩኒቨርስቲ በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ (LLB) ያላቸው ሲሆን ሕንድ ሀገር ከሚገኘው ኢንድራ ጋንዲ ዩኒቨርስቲ በፖለቲካል ሳይንስ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም በአ.አ.ዩ ለሌላ ሁለተኛ ዲግሪ ሰላምና ደኅንነት (Peace and Security) እያጠኑ ይገኛሉ፡፡ የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት እየወሰደ ያለውን ሕግ የማስከበር እርምጃ ተከትሎ የተለያዩ ጥያቄዎች አንስተንላቸው ቆይታ አድርገናል፡፡ እንድታነቡት እንጋብዛለን፡፡ መልካም ንባብ!



*ጊዜዎን ሰውተው፤ከዜጎች መድረክ ጋር ቆይታ ለማድረግ ፈቃደኛ ስለሆኑ እናመሰግናለን፡፡*

እድሉን ስለሰጣችሁኝ፤ እኔም አመሰግናለሁ፡፡

*መንግሥት፣ መከላከያ ሠራዊት ሕግ ለማስከበር እርምጃ እየወሰደ እንዳለ እየገለፀ ይገኛል፡፡አንዳንድ አካላት እየተወሰደ ያለው እርምጃ ሕግ የማስከበር አይደለም፡፡ የትግራይ ሕዝብ ላይ የተደረገ‹‹ወረራ››ነው ሲሉ ይገልፁታል፡፡በተጨማሪም ኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አላት ለማለት አይቻልም፡፡ አሁን ያለው መከላከያ ሠራዊት የአንድ ፓርቲ(ብልፅግናን) አገልጋይ ሆኗል ይላሉ፡፡እየተወሰደ ያለው እርምጃስ እንዴት ነው የሚረዱት?*

በኔ እምነት የሀገር መከላከያ ሠራዊት ማለት የአንድ ፓርቲ ንብረት መሆን የለበትም ብዬ ነው የማምነው፡፡ ኢዜማም መከላከያ ሠራዊት የአንድ ፓርቲ ንብረት ሊሆን አይገባም ብሎ ነው የሚያምነው፡፡ የመከላከያ ሠራዊትን በስልጣን ላይ ካለው ቡድን ጋር አቆራኝቶ መመልከት በሀገራችን የተለመደ አካሄድ ነው፡፡ለምሳሌ በደርግ ግዜ የነበረውን የመከላከያ ሠራዊት የደርግ ሠራዊት፤በኢህአዴግ ጊዜ ያለውንም የኢህአዴግ ሠራዊት፤አሁን ደግሞ ብልጽግና ስልጣን ስለያዘ የብልጽግና ሠራዊት ይባላል፡፡ ይሄ ትክክለኛ ገለፃ አይደለም፡፡

መከላከያ ሠራዊት የሀገርን ሉአላዊነትና አንድነትን የሚያስጠብቅ ተቋም ሆኖ እንዲገነባ ከፈለግን ከፓርቲ ፖለቲካ ነፃ መሆን እንዳለበት የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ አሁን ያለው መከላከያ ሠራዊት ነፃ ነው ወይ ብለህ ጥያቄ ብታነሳልኝ በሕወሓት ጊዜ ከነበረው ሆን ተብሎ መከላከያውን በቁጥጥር ስር ለማድረግ ተብሎ የተሰራው ስብስብ የሆነ ስራ ስላለ መከላከያው ችግር ሊኖርበት ይችላል፡፡ይህንን ችግር በማረም መከላከያው ወደ ትክክለኛው ጎዳና እንዲጓዝ መደረግ አለበት፡፡መከላከያ ሠራዊትን ከአንድ ፓርቲ ጥገኝነት፣ከአንድ ፓርቲ ታዛዥነት ሙሉ በሙሉ መነጠል መቻል አለብን፡፡ ይሄንን ማድረግ የምንችለው ሁላችንም መከላከያው የኔ ነው ያልን እንደሆነ ነው፡፡ ይህም ማለት መከላከያው የማንም አይደለም፤የብልፅግና አይደለም፤የሕወሓት አይደለም፤የኔ ነው ብለን መከላከያው የራስ መተማመን እንዲሰማው ማድረግ መቻል ማለት ነው፡፡

ሕግ የማስከበር ሥራ ነው አይደለም?የሚለውን ለማየት ከመነሻው ለዚህ ያበቃን ነገር ምንድ ነው?የሚለውን ማየት ነው መልስ የሚሰጠን ብዬ አስባለሁ፡፡ኢሕአዴግ ውስጥ በተደረገ ንግግር፣ድርድር ወይም ሌላ ስያሜ ልንሰጠው የዛሬ ሶስት ዓመት ለውጥ መጣ፡፡ ይህንን ለውጥ እንደመሰላል ተጠቅመው የሆኑ አካላት ስልጣን ላይ ወጡ፡፡አሁን በስልጣን ላይ ያለው‹‹ብልፅግና››የሚባል ፓርቲ ተፈጠረ፡፡ በዚህ ምክንያት ሕወሓት የሚባለው ቡድን ጠቅልሎ ትግራይ ክልል ገባ፡፡

በትግራይ ክልል ውስጥ ሕወሓት ከትግራይ ክልል አጥቶት የነበረውን ተቀባይነት ለማግኘት በጣም ብዙ ስራዎች እየሰራ እንደቆየ ግልጽ ነው፡፡ ‹‹ኢትዮጵያን እናለማለን ብለን እናንተን በድለናችኋል››በማለት ሕዝቡን ይቅርታ እስከመጠየቅ ድረስ ደርሷል፡፡ በመንግሥት ላይ ያምፃሉ ብሎ ያሰባቸውን አካላት በመደገፍ ሰላማዊ ዜጎች ላይ ጭምር አደጋ እንዲደርስ በማድረግ ሲደግፍ ነበር፡፡ ይህም በማስረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡

ማዕከላዊ መንግሥቱን እንደማይቀበል በተግባር አሳይቷል፡፡ምሳሌ ለማቅረብ ያህል የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሀገር አቀፉን ምርጫ በ2012 ዓ.ም ማድረግ አይቻልም ብሎ ያስተላለፈውን ውሳኔ ተላልፈው ምርጫ ማድረጋቸው የሚታወስ ነው፡፡ምርጫ ካደረጉ በኋላ የልብ ልብ ተሰምቷቸው ማዕከላዊ መንግሥቱን ሕገ-ወጥ ስለሆነ አንቀበለውም እስከማለት ደርሰዋል፡፡ማዕከላዊ መንግሥቱ በተለያዩ ምክንያቶች ምንም አይነት እርምጃዎች ሲወስድ አልታየም፡፡ይሄም እንደገና የልብ ልብ ብሰጥቷቸው አሁን ደግሞ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ላይ የተቃጣ ጥቃት አድርሰዋል፡፡

*ጥቃቱን ቀድሞ ያደረሰው ማነው? ተብሎ ለሚነሳው ጥያቄም የራሳቸው ሰዎች በሚዲያ ወጥተው የማዕከላዊ መንግሥቱ ወደ ትግራይ ክልል እየተጠጋ ስለሆነ ቅድመ መከላከል ነው ያደረግነው ብለው ተናግረዋል፡፡ስለዚህ ማዕከላዊ መንግሥቱ ይሄ ሁሉ ሲሆን ዝም ማለቱ በተወሰነ መልኩ የሚደነቅ ቢሆንም፣መከላከያ ሠራዊት ላይ ጥቃት ሲፈጸም ግን ማዕከላዊ መንግስቱ ጥቃቱን በፍፁም ዝም ብሎ ሊያልፈው አይችልም፡፡*

*እርምጃው ሕግ የማስከበር ነው ተብሎ እንዴት ሊገለፅ ይችላል ታዲያ?*

ሕግ ማስከበር ስንል መጀመሪያ ሁሉም ሰው ከሕግ በታች እንደሆነ ማሳየት አለብን፡፡አንድ ሀገር የራሱ መተዳደሪያ ሕግ አለው፡፡ከሱ በታች ሁሉም ሰው የመንግሥት ባለስልጣንም ሆነ የክልል አስተዳደር፣ ፓርቲም ሆኑ ግለሰቦችም ከሕግ በታች መሆናቸውን ማወቅ አለባቸው፡፡የሀገር ሉዓላዊነትን የሚያስከብረው መከላከያ ሰራዊት ስለሆነ መከላከያ ሠራዊትን መንካት ማለት የሀገር ሉዓላዊነት መድፈር ማለት ነው፡፡ስለዚህም ይህንን አይነት ተግባር ማድረግ በማይችሉበት መልኩ እርምጃ መወሰድ አለበት ብዬ ነው የማምነው፡፡ይህንን ማድረግ ደግሞ ሕግ ማስከበር ነው፡፡ሌላ ስም ልታወጣለት አትችልም፡፡ሕግ የማስከበር እርምጃው እስከ ጥግ ተጠናቆ ሕወሓትም ከሕግ በታች እንደሆነ በሚያሳይ መልኩ መጠናቀቅ አለበት ብዬ ነው የማስበው፡፡

*አሁን እየተወሰደ ያለው እርምጃ ሕግ የማስከበር አይደለም፡፡በሁለት ድርጅቶች (ሕወሓትና ብልፅግና)መካከል ያለ ግጭት ነው፡፡በሁለቱ ድርጅቶች ጸብ ንፁሀን ዜጎች ዋጋ መክፈል የለባቸውም፡፡ ንፁሀን ዜጎች ሰለባ መሆን ስለሌለባቸው የተፈጠረው ችግር በድርድር ነው እልባት ሊበጅለት የሚገባው በማለት አስተያየታቸውን የሚሰነዝሩ አሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ድርድር የሚባለው አማራጭ ሕወሓትን በተለየ ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡ መሰል ችግርን በድርድር እንፍታ ብሎ ሙከራ ማድረግ በሀገሪቱ ስርዓት አልበኝነት እንዲሰፍን በር መክፈት ነው የሚሉ አሉ፡፡ መከላከያ ሠራዊቱ ላይ ጥቃት የሰነዘረ ቡድን ጋር ቁጭ ብሎ መነጋገር ለስርዓት አልበኝነት በር ከፋች አይሆንም?*

በሕወሓትና በብልጽግና በጣም ብዙ ድርድሮች ተካሄደዋል፡፡በግልፅ የምናውቃቸውን ለመግለፅ ያህል የትግራይ ክልል ነጋዴዎች ይህንን ድርድር ለማድረግ እንደሞከሩ በይፋ የተነገረ ነገር ነው፡፡ የሀገር ሽማግሌዎች ሁለት፣ሶስት ጊዜ እንደሞከሩ ሰምተናል፡፡የሀይማኖት አባቶች ሁለቱን አካላት ለማነጋገር ተደጋጋሚ ሙከራዎች አድርገዋል፡፡ የሀይማኖት አባቶቹ እንደውም ትግራይ ክልል ሄደው ከአየር ማረፊያ እንዲመለሱ መደረጋቸው የሚታወስ ነው፡፡ለድርድር ፍቃደኛ ያልሆነው ሕወሓት ነው፡፡ ብሔራዊ ውይይት ይኑር ይል ነበር፡፡ሀገራዊ ውይይቶች ለማካሄድ ተሞክሯል፡፡ በትክክለኛው መንገድ የተካሄዱ አይደሉም በሚለው እኔም እስማማለሁ፡፡ ግንለማድረግ ሙከራ ተደርጓል፡፡እነዚህ ውይይቶች ውስጥ ሕውሓት አልነበረም፡፡ራሱን አግልሎ ነበር፡፡ በውይይቶቹ ላይ ላለመገኘቱ ያቀርብ የነበረው ምክንያትም ማዕከላዊ መንግሥቱ ይሄንን (የማወያየት) ስልጣን የለውም የሚል ነው፡፡ሀገራዊ ድርድር እና ውይይት ይደረግ የሚል አካል ይህንን ማድረግ የሚችለው ማዕከላዊ መንግሥቱን እውቅና ሰጥቶ ነው፡፡ ሕወሓት እውቅና ሳይሰጥ ነው ውይይት ይካሄድ ሲል የነበረው፡፡

ሌላው ማየት ያለብን የሕወሓትን ተፈጥሮ ነው፡፡ሕወሓት እስከ ዛሬ በታሪኩ ለእውነተኛ ድርድር እና ለእውነተኛ ንግግር ክፍት ሆኖ አያውቅም፡፡በብልጣ ብልጥነት ንግግሮችንና ድርድሮች ላይ የበላይ ▶


አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ህዳር 9 ቀን 20113 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ሆኖ መውጣት ነው የሚያስበው እንጂ እውነተኛ ድርድር በሕወሓት አይታወቅም:: ሕውሓትን የመሰረቱት ታጋዮች እንደሚነግሩን ለድርድር የጠሯቸውን ሰዎች የሚያርዱና የሚረሽኑ የነበሩ ሰዎች መሆናቸውን ነው:: ለድርድር የጠሯቸውን ሰዎች አሁን መከላከያ ላይ እንዳደረጉት ለሊት ረሽነው የበላይነታቸውን ያስጠብቁ የነበሩ ናቸው::የቅርብ ታሪክ አንስተን በምርጫ 97 ያደረጉትን ማየት ይቻላል:: ‹‹እንነጋገር እንደራደር››ብለው የቅንጅትን አመራሮች እስር ቤት ነው ያጓሯቸው:: በወቅቱ ራሳቸው ባመኑት እንኳ ሁለት መቶ በላይ ሰዎች በአደባባይ ረሽነዋል::ከልባቸው ድርድርን የሚያምኑ ሰዎች አይደሉም::

*የአውሮፓ ህብረት ሕወሓትንና ብልፅግናን ለማሸማገል ጥረትአድርጎ ነበር::ሕወሓት ለመደራደር በወቅቱ ካቀረበው ቅድመ ሁኔታ አንዱ ጠቅላይ ሚንስትር አብይ አህመድ ከስልጣን ወርደው የሽግግር መንግሥት መመስረት አለበት የሚል ነው::በብልፅግና በኩል ደግሞ ቀርቦ የነበረው ቅድመ ሁኔታ ሕወሓት አካሄድኩት ያለው ምርጫ እንዲሰርዝ የሚል ነበር::እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች በማጤን ማን መደራደር ፈልጓል ማንስ አልፈለገም የሚለውን ማየት አይቻልም?*

የበላይነትን ይዘህ የምታደርገው ድርድር፤ድርድር አይደለም::የትግራይን ሕዝብን አግተህ ይዘህ፤ትግራይ ክልል ያለሁት እኔ ነኝ፤ይሄን ያህል ሚሊሻ አለኝ፤ከፈለጋችሁ ሰላም እንሁን ካልሆነ ሀገር እበጠብጣለሁ፤ሀገር አፈርሳለሁ ማለት.... ለአፋቸው እንኳን አይሰቀጥጣቸውም:: እኛ ከሌለን ሀገር እናፈርሳለን ነው ሲሉት የነበረው::እነሱ ሀገር ለማፍረስ ያላቸውን ወኔና ቁርጠኝነት ያህል ኢትዮጵያን ለማስቀጠል ወኔና እልህ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ አለ::

አንድ እውነተኛ ድርድር የፈለገ ሰው የማያደርገው ነገር ቅድመ ሁኔታ ማስቀመጥ ነው:: ሕወሓት ከ45 ዓመት በላይ ያስቆጠረ ድርጅት እንደሆነ ይታወቃል:: በዚህ እድሜው ሁሉ ለድርድር ዝግጁ እንዳልሆነ ነው::ከምርጫው በፊት በሽግግር መንግስት ስም መሳርያና አንድ ክልል ስለያዘ የትግራይ ሕዝብን በማገትና ሕዝቡን እንደመደራደርያ አቅርቦ በማዕከላዊ መንግሥት ስልጣን መያዝ ነው አላማው::

*ሕግ የማስከበር እርምጃው ከማንም በላይ የሚጠቀመው የትግራይ ህዝብ ነው የሚሉ አሉ::ምክንያቱም ባለፉት 30 ዓመታት ያህል ከፍተኛ የሆነ የጭቆና ቀንበር ውስጥ ነበር::*

‹ ሕወሓት አምባገነን ፓርቲ ነው ::ከራሱ ጥቅምና ከግለሰቦች ጥቅም ባለፈ ለትግራይ ሕዝብም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የቆመ ፓርቲ አይደለም::ብዙ ግዜ መቀሌ ተመላልሻለሁ:: አፈናው በጣም ከባድ ነው:: ሕዝቡ ለማውራት ይሳቀቃል::በሕወሓት አገዛዝ በጣም ብዙ መስዋዕትነት የከፈለና አሁንም በድህነት እየማቀቀ የሚኖር ሕዝብ ነው::በስሙ ነግደው ያለውን ሁሉ ዘርፈውታል::››

*በዚህ ሂደት ሕወሓትን ከሕግ በታች ማድረግ የሚቻል ከሆነ የትግራይ ሕዝብ ተጠቃሚ ይሆናል ይላሉ እነዚሁ ወገኖች::ሌሎች ደግሞ የትግራይ ሕዝብ ምንም ተጠቃሚ አይሆንም::እንዲያውም የትግራይ ሕዝብ ራሱ በራሱ የማስተዳደር መብቱን ይነጠቃል ይላሉ:: በነዚህ ሁለት አስተያየቶች ላይ ምላሽዎትን ቢሰጡን?*

ሕወሓት አምባገነን ፓርቲ ነው ::ከራሱ ጥቅምና ከግለሰቦች ጥቅም ባለፈ ለትግራይ ሕዝብም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የቆመ ፓርቲ አይደለም::ብዙ ግዜ መቀሌ ተመላልሻለሁ:: አፈናው በጣም ከባድ ነው:: ሕዝቡ ለማውራት ይሳቀቃል:: በሕወሓት አገዛዝ በጣም ብዙ መስዋዕትነት የከፈለና አሁንም በድህነት እየማቀቀ የሚኖር ሕዝብ ነው::በስሙ ነግደው ያለውን ሁሉ ዘርፈውታል:: የትግራይ ኢኮኖሚ እንኳን በጥቂቶች እጅ ነው ያለው::ሕወሓት ከጫንቃው ላይ ሲነሳ የትግራይ ሕዝብ በነፃነት መናገር የሚችልበት፣የሚያስተዳድሩትን ራሱ የሚመርጥበት ሁኔታ ነው የሚፈጠርለት ብዬ ነው የማምነው::

*ሕግ የማስከበር እርምጃው ንፁህን ሰለባ እንዳይሆኑና እንዳይጎዱ ሕግ የማስከበር እርምጃው ምን አይነት መንገዶችን መከተል አለበት?*

አሁን የተፈጠረው ግጭት እና በሱ ምክንያት የመጣው ሕግ የማስከበር ዘመቻ ንፁህ ሰው በማይሞትበት መልኩና አደጋ በማይደርስበት መልኩ እንዲጠናቀቅ የሁላችንም ምኞት ነው::ከጥቂቶች በቀር (እንደ ሕወሓት ያሉ) ጦርነትን ፈልጎ የሚገባበት ቡድን ያለ አይመስለኝም::በዓለም ላይ በተለያዩ ከተሞች ላይ የተደረጉ ተመሳሳይ እርምጃዎችን ስናይ በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ሰዎች ላይ ጉዳት መድረሱ የሚቀር አይሆንም ::በትግራይ ክልል ይሄ እንዲሆን የሚያደርገው ደግሞ ሕወሓት ነው::ምክንያቱም ሕዝቡን አግቶ በመያዝ ሕዝቡ ውስጥ ነው የተቀመጠው::ሕዝቡ መሀል ተቀምጦም ነው ትንኮሳ እያካሄዱ ያለው:: ይህን ለማስቆም በሚደረግ ጥረት ውስጥ ንፁሀን ላይ አደጋ መድረሱ የሚቀር አይመስለኝም::አደጋውን ሙሉ ለሙሉ እንዳይደርስ ማድረግ ባይቻልም የሚደርሰውን አደጋ መቀነስ የሚቻል ይመስለኛል::ንፁኀን ላይ አደጋ ከሚደርስ ወንጀለኞች ቢያመልጡይ ሻላል::የዛን ያህል‹‹ሪስክ››ወስደው ንፁሀንን መጠበቅ አለባቸው ብዬ ነው የማምነው:: የሚወሰዱ እርምጃዎች በጣም የታቀደባቸውና የታሰበባቸው መሆን አለባቸው:: ሕወሓትና ሕወሓታውያን ላይ ብቻ ነው ኢላማ ሊደረግ የሚገባው::

*የሰሜን እዝ ላይ እርምጃ በመውሰድ ተሳትፎ አድርገዋል ተብለው የተጠረጠሩ የመከላከያ ሰራዊት አባላት የጊዜ ቀጠሮ ፍርድ ቤት ቀርበዋል::በሀገር መከዳት የተጠረጠሩት የጦሩ የቀድሞ አባላት እንዴት ሲቪል ፍርድ ቤት መቅረብ አልነበረባቸውም::የጦር ፍርድ ቤት ነው መቅረብ የነበረባቸው በሚል አስተያየታቸውን የሚሰነዝሩ አሉ:: እነዚህ የመከላከያ ሠራዊት አባላት የጦር ፍርድ ቤት ነው መቅረብ የነበረባቸው ወይስ የሲቪል ፍርድ ቤት?*

‹‹ማንኛውም በመከላከያ ሠራዊት ላይ የሚደርስ ጥቃት ሁሉ በጦር ፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም:: ይሄኛውን ለየት የሚያደርገው ግን ሀገር የመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች የመከላከያ ሠራዊት አባል የነበሩ ሰዎች ላይ የፈፀሙት ጥቃት በመሆኑ ነው::››

ማንኛውም በመከላከያ ሠራዊት ላይ የሚደርስ ጥቃት ሁሉ በጦር ፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም::ይሄኛውን ለየት የሚያደርገው ግን ሀገር የመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች የመከላከያ ሠራዊት አባል የነበሩ ሰዎች ላይ የፈፀሙት ጥቃት በመሆኑ ነው::እንዲህ አይነት አጋጣሚ (የመከላከያ አባል ሆኖ በመከላከያ ላይ ጥቃት የሚያደርስ ከሆነ)ሲፈጠር ጉዳዩ በጦር ፍርድ ቤት መታየት እንዳለበት ነው ሕጉ የሚደነግገው::

*የፌደራል መንግሥቱ በጀመረው ሕግ የማስከበር ዘመቻ ውስጥ በፕሮፓጋንዳና*



*በዲፕሎማሲ በጣም ብልጫ ተወስዶበታል የሚሉ አሉ:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዘመቻው ሕግ የማስከበር ዘመቻ መሆኑን ከማስረዳት አንፃር የሕግ ባለሙያዎች የሚኖራቸው ሚና ምንድነው ብለው ያስባሉ?*

መንግሥት ብልጫ ተወስዶበታል ወይ?ከሚለው ብንጀምር በኔ እምነት አሁን የዲፕሎማቲኩ ማኅበረሰብ እያለ ያለው ተነጋገሩ ግጭት አያስፈልግም ነው::የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰቡ ይህንን (ተነጋገሩ) በማለቱ ከሆነ መንግሥት ብልጫ ተይዞብታል እያልን ያለነው ትክክል አይመስለኝም ::የሆነውንም ነገር እነሱም (ሕወሓታውያን)እያካዱት አይደለም::እኛ ላይ እርምጃ ሊወስዱ ስለሆነ ቀድመን እርምጃ ወሰድንባቸው ነው ያሉት::መከላከያ እርምጃ ሲወሰድበት እጁን አጣጥፎ ይመልከት የሚል አካል ያለ አይመስለኝም::የአሜሪካ መንግሥት ተወካይ ሕወሓት፣ ኤርትራ ላይ የወሰደውን ጥቃት ገልጾ ይሄንን እያደረገ ያለው ግጭቱን ዓለማአቀፍ ለማድረግ ስለሆነ ይሄንን ማስቆም እንደሚገባ ገልጿል::

ምክትል ጠ/ሚ እና የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር ደመቀ መኮንን፣የተለያዩ አፍሪካ ሀገራት እየተጓዙ ሕግ የማስከበር እርምጃው ያለውን አላማ እያስረዱ ነው የሚገኙት:: ይህን እያደረጉ ያሉት የዲፕሎማሲ የበላይነት ለማግኘት ይመስለኛል::እያንዳንዱ ዜጋ አምባሳደር ነው ለሀገሩ ብዬ ነው የማምነው::ስለዚህ ይሄን ሥራ (እየተወሰደ ያለውን ሕግ የማስከበር እርምጃ ማብራራት)መሥራት ይገባዋል:: በተለይ በተለይ በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን ይሄንን እንዲያደርጉ ጥሪ መቅረብ አለበት ብዬ አስባለሁ::እንደ ኢዜማ ለሀገር አንድነት እና ለሀገር ሉዓላዊነት ቅድሚያ እንሰጣለን ብለው በፕሮግራማቸው ያስቀመጡ ፓርቲዎችም ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የሆነውን ነገር ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ በማሳወቅ እና መረጃ እንዲኖራቸው በማድረግ ሀገር ከዲፕሎማሲ ማግኘት ያለባትን ጥቅም ማግኘት አለባት ብዬ አስባለሁ::

*በኔ በኩል ጥያቄዎቼን አገባድጃለሁ::ያልተነሳ ሀሳብ ካለ እድል ልስጥዎትና እንሰነባበት::*

እንደዚህ አይነት ሁኔታዎች መከሰታቸው በጣም የሚያሳዝን ነው::እንደ ሀገር ባይመጡ የምወደው ነገር ነው::የሰው ህይወት ማጣታችን የሚያሳዝን ነገር ነው:: እንደዚህ ያሉ አጋጣሚዎች መጥፎነታቸው እንዳለ ሆኖ ግን እንደ ሀገር የሚሰጡን እድል አለ ብዬ አምናለሁ::ፍረንጆቹ በመጥፎ ነገር ውስጥ የምታገኘው ጥሩ ነገር አለ ይላሉ:: ሕግ የማስከበር እርምጃው ሁለት ጥሩ ነገሮች አምጥቷል ብዬአስባለሁ::ኢትዮጵያዊ ማንነት የሚባለው ማንነት እንዳለ አይቼበታለሁ::ከተለያዩየ ሀገሪቱ ክልል፣ሀገር ተነካች የመከላከያ ሠራዊት ተነካ ብሎ እየተነሳ ያለው ሀይል ቀላል እንዳልሆነ አይተናል::ስለዚህ ተስፋ ሰጪ ነገሮች አይቼበታለሁ::ሌላው ትምህርት አግኝተንበታል ብዬ የማስበው፤ ፌደራሊዝም ማለት በዘር መስመር ብቻ የሚሰራ አከላለል ተደርጎ እንሰበክ የነበረው ነገር ምን ያህል ውሸት እንደሆነ ምን ያህል ለሀገር አጥፊ እንደሆነ ማየት ችለናል ብዬ አስባለሁኝ::የምንማር ከሆነ እንደ ሀገር ይሄ ትልቅ የመማሪያ እድል ነው ብዬ አስባለሁ:: የክልሎች የሚሊተሪ አቅም ማዕከላዊ መንግሥቱን የሚገዳደር መሆን የለበትም:: የክልል ልዩ ሀይልን በሚመለከት ያለን አተያይ መፈተሽ አለብን::ብዙ ጊዜ የምንማረው ከሌሎች ሀገራት ስህተት ነው:: ከራሳችን ስህተት የምንማርበት ጥሩ አጋጣሚ ተፈጥሯል ብዬ አስባለሁኝ::የምንማርበት እንዲሆን ተስፋ አድርጋለሁ::

# ነፃ ሀሳብ

ማሳሰቢያ:- ይህ ፅሁፍ የፀሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚወክለው!

# ተመራጩ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት እና የአፍሪካ ፖሊሲያቸው ቀዳሚ ምልከታ

በይመስገን መሳፍንት

የሦሥት መቶ ዓመታት ገደማ ታሪክ ብቻ ያላት አሜሪካ 45 ፕሬዝዳንቶች ተፈራርቀውባታል :: አንድ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የሚሰየመው ለአራት ዓመታት ብቻ ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ መመረጥ አይችልም ሲል ገዢ ህጋቸው ያስቀምጣል:: በዚህ መሰረት ለሁለተኛ እና ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ውድድር የገቡት 45ኛው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ዶናልድ ትራምፕ በተቀናቃኛቸው መራር ሽንፈት አስተናግደዋል:: የዴሞክራቱ ፓርቲው እጩ ጆ ባይደን ለሶስተኛ ጊዜ በገቡበት የአሜሪካ ፕሬዝዳንትነት ውድድር ድል ማስመዝገባቸው ሳያንስ ብዙ ጉልህ ታሪክ በማስመዝገብ በዓለ ሲመታቸውን ይጠባበቃሉ:: የሸንብራ ፍሬ የምታክለውን የዴልዌር ግዛትን መወከላቸው ሳያንስ በ30 ዓመታቸው በተወከሉበት የአሜሪካ ሴኔት ወጣቱ ሴናተር በሚል ታሪክ እንደጻፉ ሁሉ አንጋፋው ፕሬዝዳንት በመሆን ወደ ነጩ ቤተመንግስት ሊያመሩም ቀናት ብቻ ይቀሯቸዋል:: በቅርቡ ሰባ ስምንተኛ የልደት በዓላቸውን የሚያከብሩት ጆ ባይደን ምክትል ፕሬዝዳንት አድርገው ወደ ውድድር ያስገቧቸው ካሜላ ሐሪስም የመጀመሪያዋ ሴት ምክትል ፕሬዝዳንት ናቸው፤ እንዲሁም ጥቁር አሜሪካዊ በመሆን እና ከስደተኛ ቤተሰብ የተፈሩ በመሆን አዲስ ታሪክ ያስመዘግባሉ::

እኚህ ተመራጭ ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት በአፍሪካ አህጉር ዙሪያ ከዚያ ከፍ ሲልም በአገራችን ኢትዮጵያ ዙሪያ ምን አይነት የፖለቲካ ምልከታ፣ እንዴትስ ያለ የውጭ ግንኙነት ዕቅድ ይኖራቸዋል የሚለውን በዚህ ጽሁፍ እንመለከታለን:: ከዚያ አስቀድመን ግን የፖለቲካ ታሪካቸው እና ያለፈ ዘመን የፖለቲካ እሳቤዎቻቸውን በጥቂቱ በመዳሰስ እንጀምር::

### የጆ ባይደን የፖለቲካ ጉዞ

በስክራተን፣ ፔንሲልቫኒያ በኖቬንበር 20፣ 1942 እአአ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሠራተኛ ቤተሰቦቻቸው ተወለዱ:: እስከ 13 ዓመታቸው እዛው ፔንሲልቫኒያ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የቆዩ ቢሆንም ከቤተሰቦቻው ጋር እ.ኤ.አ በ1957 ወደ ዴልዌር ግዛት አቀኑ:: የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን



በታሪክ እና ፖለቲካ ሳይንስ በሁለት ሜጀር በ1965 አገኙ:: ከዚያም ወደ ሕግ ትምህርት ቤት በመግባት በ1968 አጠናቀው የሕግ የሙያ ፍቃድ ይዘዋል:: ራስን በመግለጽ ብቃት እና በአነቃቂ የንግግር ችሎታቸው የሚታወቁት ጆ ባይደን በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ስለ ሕገ መንግሥት ሴሚናር በመስጠት ይታወቃሉ::

የሕግ ተማሪ በነበሩት ወቅት ኔይላ ሐንተር ከተባለች ሴት ጋር የፍቅር ግንኙነት በመጀመር ወደ ትዳር አምርተዋል:: ሦሥት ልጆችን ከኔይላ ቢያፈሩም በ1972 ሚስታቸው እና አንድ ልጃቸውን በመኪና አደጋ አጥተዋል :: ይህንን ዕለት በአሳዛኝነቱ የሚያስታውሱት ጆ ባይደን የህልፈተ ህይወታቸውን ቀን ለመዘከር በየዓመቱ ዲሴምበር 18 ስራ አይሰሩም :: ፖለቲከኛ ሆነው ወደ ሴኔት ካመሩ በኋላ በወንድማቸው ገፋፊነት የተዋወቋትን ጂል ትሬሲን በማግባት አሽሊ የተሰኘች ልጅ አግኝተዋል:: እስካሁንም ከአስተማሪዋ ጂል ባይደን (ዶክተር) ጋር በትዳር ይኖራሉ::

እ.ኤ.አ ከ1979-2009 ዴልዌርን በሴኔት የወከሉት ጆ ባይደን በ2008 ከባራክ ኦባማ ጋር ለምክትል ፕሬዝዳንትነት በመወዳደር ለ8 ዓመታት አገልግለዋል:: ከዛ ቀደም በሴኔቱ የሕግ ኮሚቴን እና የውጭ ግንኙነት ኮሚቴን መርተዋል:: በ1979 አንዋር ሳዳት የግብጽ እስራኤልን ስምምነት ሲፈርሙ ጆ ባይደን በስፍራው ነበሩ:: ከ60 በመቶ በላይ ድምጽ በተደጋጋሚ በማግኘት 6 ጊዜ ለሴኔት ተመርጠዋል:: በሊበራል አቋማቸው የሚታወቁት ጆ ባይደን በአሜሪካ ኮንሰርቫቲቭ ዩንየን (ACU) በሚወጣው ደረጃ 13 በመቶ ብቻ ወግ አጥባቂ ሲባሉ በአሜሪካንስ ፎር ዴሞክራቲክ አክሽን (ADA) የደረጃ ውጤት 72 በመቶ ሊበራልነታቸው ተመስክሮላቸዋል ::

በ2008 በምክትል ፕሬዝዳንቶች የምርጫ ክርክር ሳራ ፔለን ላይ በ2012 በፖል ራያን ላይ አመርቂ የክርክር ችሎታቸው ጎልቶ የወጣ ሲሆን ደጋግመው በሞከሩት የፕሬዝዳንትነት ውድድርም ለውስጠ ፓርቲ ተቀናቃኞቻቸው ፈተና ነበሩ:: ከዶናልድ ትራምፕ ጋር ሁለት ጊዜ ለክርክር የቀረቡ ሲሆን የዶናልድ ትራምፕ ረባሽ ስነ-ባህሪ ጥላ ቢያጠላባቸውም ግልጽ ሕግ የማስከበር እና የማኅበራዊ ፖሊሲዎች እንዳላቸው አስምረው ልዩነታቸውን አሳይተዋል::

### የካሜላ ሐሪስ የፖለቲካ ጉዞ

በኦክላንድ፣ ካሊፎርኒያ በኦክቶበር 20፣1964 የተወለዱት ካሜላ ሐሪስ በ2016 ካሊፎርኒያን ወክለው ለሴኔት ሲመረጡ የዘር ሐረጋቸው የሕንድ እና የጃማይካ የሆነ የመጀመሪያዋ ሴናተር ሲሆኑ አፍሪካ አሜሪካዊት ሴት በመሆንም ሁለተኛዋ ሆነዋል:: ከሐዋርድ ዩንቨርሲቲ በፖለቲካል ሳይንስ እና ከሐስቲንግ ኮሌጅ በሕግ የተመረቁት ካሜላ ሐሪስ ከ1990 እስከ 1998 በኦክላንድ የወረዳ አቃቤ ሕግ ሆነው አገልግለዋል:: ትልቅ እውቅና ያስቸራቸውን የቡድን ጠብ፣ የሴቶች ጥቃት እና የአደንዛዥ እጽ ዝውውር ክሶችን በሙሉ በድል የመወጣቸው ዜና በካሊፎርኒያ እንዲናኙ አደረጋቸው:: በ2010 የካሊፎርያ አቃቤ ሕግ ሆነው በጠባብ ልዩነት ተመረጡ:: በባራክ ኦባማ ፕሬዝዳንትነት ዘመን ያወጡት (Smart on Crime, 2009) መጽሐፋቸው ሕግን የማስፈንን ሥራ በዘመናዊ መልኩ ከፖለቲካ ተጽዕኖ በተፋታ መልኩ በመከወን እንደ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ሲባል የተሞካሸ ነበር::

በ2012 የዴሚክራቶች ኮንቬንሽን ያደረጉት ንግግር ተጠባቂ ሴት እንዲሆኑ አድርጓቸዋል:: የተጠበቀውም ሳይዘገይ እውን ይሆን ጀመር:: በ2016 ለሴኔት መመረጣቸው ሳያንስ በ2020 የፕሬዝዳንት ምርጫ ለመወዳደር በቅድመ ውድድሩ ለውስጠ ፓርቲ ሩጫ ተሰየሙ:: በዚህ ወቅት ያነሷቸው ጽንሰ ሀሳቦች በቅድመ ምርጫው ጎልተው የወጡት ጆ ባይደን በምክትልነት አብረዋቸው እንዲወዳደሩ ዓይን ውስጥ የገቡበት መሆኑ አያጠራጥርም:: በ2017 በሴኔቱ ፊት የአሜሪካውን ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ጄፍ ሴሽንስ ሲያፋጥጡ የበለጠ እውቅና የተቸራቸው ካሜላ ሐሪስ ተመራጭ ምክትል ፕሬዝዳንት ሆነው ከጆ ባይደን ጋር ወደ ነጩ ቤተመንግስት ማምራታቸውም ከረዥም ሩጫ በኋላ እውን የሆነ ነው::

### ተጠባቂ ስራዎች

አንጋፋው ፖለቲከኛ ጆ ባይደን እና ምክትላቸው ካሜላ ሐሪስ መንበረ ስልጣኑን ሲቆጣጠሩ ይወስዷቸዋል ተብለው ከሚገመቱ ትላልቅ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች መሀከል በጥቁር ሰዎች መብት ንቅናቄ እና በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ዙሪያ የሚካሄዱት ዋነኞቹ እንደሚሆኑ ይጠበቃል:: አሜሪካ ከዓለማቀፉ የጤና ድርጅት ለመውጣት የጀመረችውን ጥረት ማስቆም እና የኮቪድ 19 ክትባት ምርምር ስምምነትን (COVAX) የመቀላቀል ሂደትን ማፋጠን የሚጠበቁ ቀዳሚ ስራዎች ናቸው:: ከዚህ በተጨማሪ በባራክ ኦባማ ዘመን አሜሪካ በግንባር ቀደምነት የፈረመችውን የፓሪስ የአየር ንብረት ስምምነት ዳግም የጸና እንዲሆን ወደ ማድረግ እንደሚገቡም ይጠበቃል:: አሜሪካ ባለፉት አራት የዶናልድ ትራምፕ የስልጣን ዘመናት ብዙ አልገፋችበትም ተብላ የምትታማበት የታዳጊ አገራትን ዴሞክራሲያዊ የማድረግ ሥራ በጆ ባይደን ዘመን መጠናከሩም አይቀሬ ነው:: የአሜሪካን የበጀት ድጋፍ የሚጠይቁ አገራትን የማረጋጋት ሥራዎችም ብዙ እንደሆኑ መረጃዎች ያመላክታሉ::

### የውጭ ግንኙነት

አሜሪካ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት መገባደድ በኋላ ሰላም ማስከበር እና የተቀረውን ዓለም ዴሞክራሲያዊ የማድረግ ዘመቻ አሐዱ ብያለሁ ትላለች:: ከቅኝ ግዛት የተላቀቀውን ዓለም ነጻ ገበያ መር ኢኮኖሚ እና ተራማጅ የፖለቲካ ስርዓት የሰፈነበት የማድረግ መርሆ በመላው ዓለም ሲናኝ በመካከለኛው ምስራቅ፣ በእስያ ፓስፊክ እና በቀድሞዋ ሶቪየት ሕብረት እንዲሁም በሳተላይት አገሮቿ ፈተናው ከባድ እንደሆነ ታሪክ ያሳየን ህቅ ነው:: በዚህ ሁሉ የተራድኦ ስራዎችን የሚከውኑ የአሜሪካ ተቋማት ሚናቸው የጎላ ሆኖ ዘልቋል:: ይህን ከታሪክ ያስተዋለ ባለፉት አራት ዓመታት በዶናልድ ትራምፕ መሪነት የነበረው የተዳከመ የዓለማቀፍ ትብብር ሥራ የውጭ ግንኙነት ስራው ሆን ተብሎ እንዲዳከም አልያም ወደ ሌሎች የትኩረት ማዕቀፎች መቀየሩን ለመረዳት አያዳግተውም:: ለዚህም ዶናልድ ትራምፕ ከሰሜን ኮርያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን እና ከሩሲያው ቭላድሚን ፑቲን ጋር ወዳጅነት ማላቃቸውን እንደ ማሳያ መውሰድ ይቻላል:: በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ወቅት አሜሪካ በድንገት ከዓለማቀፉ የጤና ድርጅት ቀዳሚ የገንዘብ ምንጭነት ማፈግፈጓ በተቋሙ ላይም ቅሬታ ማስመዝገቧ ሌላኛው የቀነሰውን የአሜሪካ የዓለማቀፍ ትብብር ስራ ገላጭ ይሆናል :: አሜሪካንን ወደ ታላቅነት እመልሳለሁ በሚል መሪ ቃል መንበሩን የተቆናጠጡት ዶናልድ ትራምፕ ወደ አገር ውስጥ ብዙ በመመልከት ነው የውጪውን ያቀዘቀዙት የሚል ወቀሳ የሚሰነዝሩም አልታጡም :: ሆኖም ይህንን ወቀሳ ውሀ የማያነሳ የሚያደርገው የቀድሞ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪያቸው ጆን ቦልተን የሰላ ትችት ነው:: በነጩ ቤተመንግስት የነበራቸውን ቆይታ በቁጭት በማስታወስ የቀድሞ አለቃቸው ዶናልድ ትራምፕ በእውቀት ማነስ እንጂ በነጠረ የፖሊሲ አማራጭ የውጪ ግንኙነቱን እና የዓለማቀፍ ትብብርን እንደማይመሩ ብዙ ገመናቸውን ባጋለጡበት መጽሐፋቸው (The Room Where it Happened, 2019) አስቀምጠዋል::

ባሳለፍናቸው ቀናት የሚወጡ በአፍሪካ ጉዳይ የሚያጠነጥኑ ጽሁፎች እና መጽሔቶች ጆ ባይደን በዴሞክራሲ ግንባታ እና በዓለማቀፍ ትብብር ከአፍሪካ ጎን እንደሚቆሙ ጠቋሚ ናቸው:: አፍሪካን ሪፖርት እና አናዶሉ የተሰኙት መገናኛ ዘዴዎች በንግድ ትስስር እና በልማታዊ ተራድኦ አፍሪካ ከአሜሪካ ብዙ ትጠብቃለች፤ በዚህም የተቋረጡ ስምምነቶች ወደ ማስቀጠል ሳይዘገዩ ሊገቡ እንደሚገባ ጽፈዋል::

ለተመራጭ ፕሬዝዳንቱ ምክር የለገሱ ጸሀፍት እንደሚሉት ከሆነ የውጪ ግንኙነትን ለመምራት ታላላቅ ሰብዕናዎች ግንባር ቀደም ሚና አላቸው:: በዚህም የባራክ ኦባማን፣ የሒላሪ ክሊንተንን እና የጆን ኬሪን ድጋፍ ቢሹ የሚሉ ምክረ ሐሳቦች ከተቀመጡት መሀከል ናቸው:: ከዚህ ጋር በተያያዘ በጆ ባይደን ዘመን የውጪ ግንኙነትን ሊዘውሩ እና ፕሬዝዳንቱን በአማካሪነት ሊያገለግሉ ይችላሉ በሚል ከፍተኛ ግምት የተሰጣቸው ሦሥት ግለሰቦች አሉ፣ እነዚህን ከተወሰነ ስራቸው ጋር ለመተንተን እንሞክር :-

1. አንቶኒ ብሊንከን

ሊንጓ ፍራንካ ናቸው፤ በምርጫው ወቅትም የጆ ባይደን የዓለም አቀፍ ጉዳይ አማካሪ ናቸው:: አንቶኒ ብሊንከን ትውልድ እና እድገታቸው ፓሪስ በመሆኑ ከ 20 በላይ አገራት ፈረንሳይኛ ተናጋሪ በመሆናቸው በአፍሪካ ጉዳይ ቀዳሚ ሚና እንዲጫወቱ ሊመደቡ ይችላሉ የሚል ግምት አለ::

2. ሱዛን ራይስ

የጆ ባይደን የምርጫ አጋር ሆነው ምክትል ፕሬዝዳንት የመሆን ከፍተኛ ዕድል የነበራቸው ሱዛን ራይስ በውጪ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ ባላቸው የካበተ ልምድ ዳግም ትልቅ ሚና እንደሚቸራቸው ይገመታል:: በውጪ ጉዳይ መስሪያ ቤት ከ 1997-2001 የአፍሪካ ጉዳዮች ረዳት ሴክሬተሪ በመሆን ያገለገሉት ሱዛን ራይስ በወቅቱ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትን በመሸምገል ከፍተኛ ሚና ነበራቸው:: በባራክ ኦባማ መንግሥትም የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ነበሩ:: የአፍሪካን ግጭቶች ሱዛን ራይስ ሳታያቸው ማለቂያ አያገኙም እስኪባል ሚናቸውን የሚያጎሉ እንዳሉ ሁሉ እንደ መለስ ዜናዊ እና ጆሴፍ ካቢላ ያሉ አምባገነኖችን በማወደስ የሚኮንኗቸውም አሉ::

3. ኒኮላስ በርንስ

በማድሊን ኦልብራይት የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ዘመን ከፍተኛ ሚና ሲጫወቱ የነበሩት ኒኮላስ በርንስ በአፍሪካ በተለይም በማግረብ ቀጠና ባላቸው እውቀት ተጠቃሽ ናቸው:: በኔቶ እና በሩሲያ የውጪ ግንኙነት ስራዎችን በመሥራት ረዥም ልምድ አካብተዋል:: የዴሞክራቶች ውጪ ግንኙነት ፖሊሲ አሜሪካንን በተቀረው ዓለም የልማት እና የዴሞክራሲ ተልዕኮን የመደገፍ ሚና ላይ ባለው ቀጥተኛ አስተዋጽዖ የሚታወቅ ነው፤ ለዚህ ብዙዎች ኒኮላስ በርንስን ተገቢው ሰው ናቸው ይላሉ:: ሆኖም በምን ደረጃ ነው ይህንን ሚና የሚወጡት የሚለው ገና ያልተወሰነ እና ለመላምት የተጋለጠ ነው::

በአጠቃላይ ተመራጭ ፕሬዝዳንቱ ጆ ባይደን በደረጀ ሰብዕናቸው እና ሙሉ በሆነው ልምዳቸው የልዕለ ኃያሏን አገር የውጪ ግንኙነት እና የዓለማቀፍ ትብብር ከጠለሸበት አንስተው ፀአዳ እንዲያላብሱት ይጠበቃል:: በዚህም በአስቸጋሪ ወቅት እያለፈች ያለችው አገራችን ኢትዮጵያ እና መላው አፍሪካ በልማት፣ በንግድ ትስስር እና በተራድኦ ሥራዎች ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ:: በዶናልድ ትራምፕ ዘመን የተቀዛቀዘውን ግንኙነት ከማደስ ባሻገር በኮቪድ 19 ክትባት፣ በዓለማቀፍ ድርጅቶች መዋቅራዊ ለውጥ፣ በዓየር ንብረት ለውጥ ስምምነቶች፣ በመሰረተ ልማት ዝርጋታ ትብብር፣ በጸረ- ሽብር እንቅስቃሴ እና በወቅታዊ ጉዳዮች ምቹ፣ አሰሪ እና የሁሉንም ተጠቃሚነት ከግምት የከተተ የዲፕሎማሲ እና የመሪነት ስራ እንዲተገብሩ ትልቅ ተስፋ እና እምነት ተጥሎባቸዋል::

# ኢዜማ፣ አባላቶቹን በማስተባበር ‹‹ደሜን ለሀገሬ›› በሚል መሪ ቃል ለመከላከያ ሠራዊቱ ደም ለገሠ

ሕዳር 9 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)




የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) አመራርና አባላት እሁድ ሕዳር 06 ቀን 2013 ዓ.ም ‹‹ደሜን ለሀገሬ›› በሚል መሪ ቃል በብሔራዊ ደም ባንክ በመገኘት ደም ለገሱ፡፡

የደም ልገሳው መርሃ ግብር ላይ የፓርቲው ብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትና የወረዳ አባላት ተገኝተዋል፡፡ ‹‹ደሜን ለሀገሬ›› በሚል መሪ ቃል አባላቶቹን በማስተባበር ደም መስጠት ያስፈለገው ደሙንና ሕይወቱን እየሰጠ ያለውን የመከላከያ ሠራዊት ለማሰብ መሆኑን የፓርቲው ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ ተናግረዋል፡፡ በደም ልገሳው ላይ የተገኙት የፓርቲው የወጣቶች ጉዳይ ተጠሪ በኢዜማ ስም ደም ሲለግሱ አራተኛቸው መሆኑን ጠቅሰው፤ ያሁኑን ለየት የሚያደርገው መከላከያ ሠራዊቱን ታሳቢ በማድረግ የተደረገ ልገሳ መሆኑንና ሠራዊቱ እያደረገ የሚገኘውን ተጋድሎና ሕግ ማስከበር ለማገዝ ይረዳል ብለው እንደሚያምኑ ጠቅሰዋል፡፡ ተጠሪው ‹‹ይህ ልናደርገው የምንችለው በጣም ትንሹ ስጦታ ነው›› ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

የመከላከያ ሠራዊቱ እየወሰደ ያለውን ሕግ የማስከበር እርምጃ ያደነቁት ሊቀመንበሩ የሺዋስ አሰፋ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከመከላከያ ሰራዊት ጎን መቆም እንዳለበት ተናግረዋል፡፡ ‹‹የትግራይም ሕዝብም ሆነ የትግራይ ወጣት ከሌላው ኢትዮጵያዊ የተለየ ጥቅም አላገኘም›› ያሉት ሊቀመንበሩ፣ የትግራይ ሕዝብ ከመከላከያው ሠራዊት ጎን መሰለፍ እንደሚገባው ጠቁመዋል፡፡ ሕግ የማስከበር እርምጃውም በአጭር ጊዜ መጠናቀቅ እንዳለበት ገልጸዋል ፡፡

‹‹ደም መስጠታችን ለሌሎችም አርዓያ ይሆናል›› ያሉት የወጣቶች ጉዳይ ተጠሪው ያሬድ አለማየሁ፤ ወጣቱ ከመከላከያ ሰራዊታችን ጎን እንዲሰለፍ ጥሪ አቅርበው፤ ‹‹ትንሸዋን የደም ስጦታ በማድረግ ለሠራዊቱ ያለንን ድጋፍ ማሳይት እንችላለን›› ሲሉ ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡





# ሥልጠና ሊሰጥባቸው ከታቀደባቸው 16 ቦታዎች መሀል በ14ቱ ቦታዎች ላይ የተሳካ ስልጠና መሰጠት መቻሉን ድርጅት ጉዳይ ኮሚቴ ገለፀ

ሕዳር 9 ቀን 2013 ዓ.ም(የዜጎች መድረክ)

‹‹ሥልጠናውን መስጠት ባልተቻለባቸው አንዳንድ አካባቢዎች በሚቀጥለው ሳምንት ስልጠናዎቹን ለመስጠት እየሰራሁ ነው›› ድርጅት ጉዳይ ኮሚቴ

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በተለያዩ ክልሎች እየሰጠ የሚገኘው ሥልጠና ሊሰጥባቸው ካሰባቸው 16 ቦታዎች መካከል በ14 ቦታዎች ላይ ለአባላቱ ሥልጠና መስጠቱን የድርጅት ጉዳይ ኮሚቴ ለዜጎች መድረክ አስታወቀ፡፡

ኢዜማ ያዘጋጀው ሥልጠና በቀጣይ በሚደረገው ሀገር አቀፍ ምርጫ በሥሩ የሚገኙ ምርጫ ወረዳዎች የሚሰሯቸው ሥራዎች በዝርዝር እንዲያውቁ ለማድረግ ከየምርጫ ወረዳዎች ለተውጣጡ 4 አመራሮች ሥልጠናውን ሰጥቷል ፡፡ ሰልጣኞቹ ሥልጠናውን ወስደው ሲጨርሱ ወደ ወረዳቸው በመመለስ ለሌሎች አመራርና አባላት ሥልጠና እንደሚሰጡም ከድርጅት ጉዳይ ያገኘነው መረጃ ያስረዳል፡፡

ሥልጠናው ከዚህ ቀደም ለዞን አስተባባሪዎች ሲሰጥ የነበረ ስልጠና ቅጣይ ሲሆን ከምርጫ ጋር ተያይዞ የምርጫ ወረዳዎች ምን አይነት ተግባራት ላይ መሳተፍ እንደሚገባቸው፣ የምርጫ ዘመቻ ሲጀመር እንዴት መምራት እንደሚችሉ፣ የምርጫ ወረዳዎቹ ምርጫን ማሸነፍ የሚችል አቅም መገንባት ላይ እንዲያተኩሩ የሚያደርግና ሀብትና ግብዓት የማሰባሰብ ሥራ በሚሰሩበት ጊዜ በምን ዓይነት መንገድ መጓዝ እንደሚገባቸው የሚያሳውቅ ነው፡፡

ኢዜማ ያዘጋጀውን ሥልጠና በተለያዩ ክልሎች መስጠት ቢችልም በጅማ፣ በአርሲ ዞን አሰላ ከተማ፣ በባሌ ዞን ጎባ ከተማ ላይ ሥልጠና ለመስጠት የሚገባውን ቅድመ ሁኔታዎች ቢያሟላም የየአካባቢዎቹ ባለስልጣናት ከኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ብቻ ሳይሆን ከኦሮሚያ መንግሥትም ደብዳቤ መምጣት አለበት ስላሉ ሥልጠናውን ማካሄድ አለመቻሉን ለማወቅ ተችሏል ፡፡ በሚቀጥለው ሳምንት እነዚህንና ሌሎች ቦታዎችን ያካተተ ሥልጠና ለመሥጠት እየተሰራ መሆኑን ከድርጅት ጉዳይ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

# ኢዜማ እስከ ታኅሣሥ መጨረሻ ሁሉም ምርጫ ወረዳዎች የምርጫ ዘመቻውን መሸከም የሚችሉበት ቁመና ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ እየሰራ መሆኑን ገለጸ

ሕዳር 9 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) እየሰራቸው የሚገኙ ሥራዎች ከምርጫ ጋር አቆራኝቶ እየሰራ እንደሚገኝ፣ ምርጫ ወረዳዎቹም አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ በየጊዜው ድጋፍና ሥልጠና እየተሰጠ እንደሚገኝ በተጓዳኝ ኢዜማ ተደራሽ ያልሆነባቸውን ቦታዎች ተደራሽ ለማድረግ እየሰራ እንደሚገኝ ተገለጸ ፡፡

‹‹በሀገሪቱ ላይ ጠንካራ መዋቅር ስላለህ ብቻ ምርጫን አታሸንፍም፡፡ ጠንካራ እጩ፣ ጠንካራ ግብዓት የማሰባሰብ ሥራ፣ ጠንካራ የምርጫ ዘመቻ ማከናወን፣ በተጠናከረ መልኩ የሕዝብ ግንኙነት ሥራ መሥራት ወሳኝ ነገር ነው፡፡ የእነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ነው ወሳኝ የሚሆነው፣ ኢዜማም እስከ ታኅሣሥ መጨረሻ ሁሉም ምርጫ ወረዳዎች የምርጫ ዘመቻውን መሸከም የሚችል ቁመና ላይ እንዲደርሱ ሥራ እየሰራ ነው›› በማለት ፓርቲያቸው በያዝነው ዓመት ይካሄዳል ተብሎ ለሚጠበቀው 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ እያደረገ ያለውን ዝግጅት በሚመለከት የኢዜማ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ለዜጎች መድረክ አስረድተዋል፡፡

ኢዜማ በሁሉም ክልልና ምርጫ ወረዳዎች ላይ የሚገኝ በመሆኑ እነዚህን በሚፈለገው ደረጃ አደራጅቶ ብቃት ያለው እጩና ታዛቢ ማቅረብ እንዲችሉ እየሰራ እንደሚገኝ የጠቀሱት ኃላፊው፣ ኢዜማ ሥራዎችን ሲሰራ ከጸጥታ ጀምሮ የተለያዩ ችግሮች ቢያጋጥመውም ችግሮቹን በውይይት ለማለፍ እየሞከረ መሆኑን ጠቅሰው፤ በትግራይ ክልል እየተካሄደ የሚገኘው ሕግን የማስከበር ሥራ በውዴታ የተገባበት ባለመሆኑ በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቅ መደረግ እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

# ‹ ‹የትውልዱ ፕሮጀክት የሚሆነው ኢትዮጵያን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማሸጋገር ነው› ›

## የሺዋስ አሰፋ (የኢዜማ ሊቀመንበር)

ሕዳር 9 ቀን 2013 ዓ.ም(የዜናች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በፓርቲ ምዝገባና በምርጫ ሥነ ሥርዓት አዋጅ 1162/2011 የአዋጅ ማስፈጸሚያ በሆኑ መመሪዎችን ስለ እጩ አቀራረብ፣ ምርጫ ቅስቀሳ እና የውጪ ሀገራት ታዛቢዎችን በሚመለከት ሕዳር 03 እና ሕዳር 04 ቀን 2013 ዓ.ም ባካሄደው ውይይት ላይ መሳተፉን የኢዜማ ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ ለዜጎች መድረክ አስታወቁ፡፡

በውይይቱ ላይ ከእጩዎች አቀራረብ ጋር በተያያዘ የመንግሥት ሠራተኛ የሆኑ ሰዎች ‹‹ያለደሞዝ ይሥሩ›› የሚለው ተሻሽሎ የቀረበው አዋጅ በድጋሚ እንዲሻሻል ከአብዛኛው ፓርቲዎች ሀሳብ መቅረቡን የጠቆሙት ሊቀመንበሩ፣ የአንቀጹ ዋና አላማ የመንግሥት ባለሥልጣናት የመንግሥትን ሀብት ለምርጫ ቅስቀሳ እንዳይጠቀሙ ለማድረግ ቢሆንም አዋጁ የሚጎዳው የመንግሥት ባለሥልጣናትን ሳይሆን በተፎካካሪ ፓርቲዎች ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት ሥልጣን የሌላቸውን መምህራንን፣ የግብርና ባለሙያዎችን የመሳሰሉትን በመሆኑ መመሪያው መነሳት አለበት የሚል ሀሳብ ከፓርቲዎች መቅረቡንና ቦርዱሙ መመሪያውን ድጋሚ እንደሚያየው መግለጹን ለዜጎች መድረክ ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያወጣቸውን አዋጆችን ኢዜማ እንደሚቀበላቸው የጠቆሙት የሺዋስ አሰፋ፣ ‹‹ፓርቲዎች አቅማቸውን አሳድገው ወደ አዋጁ ደረጃ እና መሥፈርት መምጣት አለባቸው እንጂ አዋጁ ወደ ፓርቲዎች ደረጃ ሊመጣ አይገባም›› ያሉት ሊቀመንበሩ ቦርዱ ያወጣቸው አዋጆቹ ከዚህም በላይ ሊጠበቁ ይገባቸዋል ብለዋል፡፡ ቦርዱ ምርጫውን የሚያካሄድበት የጊዜ ሰሌዳውን አስታውቆ ፓርቲዎች ሥራ እንዲጀምሩ ፍቃድ መስጠት አለበት ሲሉ ተናግረዋል፡፡

‹‹የትውልዱ ፕሮጀክት የሚሆነው ኢትዮጵያን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማሸጋገር ነው›› ያሉት የሺዋስ አሰፋ፣ በፍጹም ኃላፊነት በመንቀሳቀስ ቀጣዩን ምርጫ የተሳካ ለማድረግ ሁሉም ቁርጠኛ መሆን ይገባዋል ብለዋል፡፡